የመ/ቁጥር 284812
18 / 12 / 2014ዓም

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ፍ/ሔር ችሎት

4ኛ ምርጫ ችሎት

ዳኞች፡- ይርጋ አይቼ

ይሄነው ከልሌ

ሰብለ ክንፈ

ከሳሽ፡- የኦሮሞ ነጻነት ንቅናቄ

ተከሳሽ፡- የኢትዮጲያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ከሳሽ ሚያዝያ 20 ቀን 2014ዓም በተፈጻፈ ክስ በተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ 573/2000 ለተከሳሽ ቦርድ በተሰጠው ስልፈጣን መሰረት በአገራቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ የምዝረገባና ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰኔ 18 ቀን 2011 ዓም ተሰጥቶታል፡፡ ከሳሽ በህጋዊ መንገድ አስፈላጊውን ሁሉ ሲፈጽም ቆይቷል፡፡ ከሳሽ አዋጁና መተዳደሪያው ደንብ መሰረት መጋቢት 15 ቀን 2-014ዓም በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው የኦሮሞ ባህል ማዕከል የስብሰባ አዳራሽ የመጀመሪያውን የጠቅላላ ጊባኤ ስብሰባ ምልአተ ጉባኤ በመሟላቱ በህጉ መሰረት ስብሰባውን አከናውኗል፡፡ ከሳሽ የጠቅላላ ጉባኤ የሚያካሂድ መሆኑን በህጉ መስረት ለተከሳሽ ቦርድ ያሳወቀ ና የተከሳሽ ቦርድ 2 ተወከዮችም በስብሰባው የተገኙ ሲሆን በእለቱ 634 የጠቅላላ ጉባኤአባላት፤ የመድረክ መሪ ፤ ፈተጋባዥ እንግዶች፤ ተጋባዥ ፓርቲዎች መሪዎች፤ የተከሳሽ መሪዎች በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባውን አከናውኗል፡፡ ከሳሽ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ምልአተ ጉባኤ የሚሟላው ቢያንስ 500 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ሲገኙ ቢሆንም ስብሰባው

ከመጀመሩ በፊት 541 አባላት መገኘታቸውን ተቆጣጣሪዎቸች ለመድረክ መሪው መግለጻቸውን፤ መድረክ መሪውም ይህንን አረጋግጦ ስብሰባውን መጀመሩን፤ ስብሰባው ከተጀመረ በኋላም ሌሎች አባላት ዘግይተው በመምጣታቸው በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባው 634 አባላት መገኘታቸው ና ስብሰባው መደረጉን፤ ከሳሽ ለተከሳሽ ይህንኑ ማሳወቁን፤ ተከሳሽ ቦርድ ግን መጋቢት 23 ቀን 2014ዓም በተጻፈ ደብዳቤ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 98(3) መሰረት በማድረግ በእቱ የተገኙ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ቁጥር 250 ብቻ መሆኑን ተወካዩቹ ገልጸውኛል ና በከሳሽ የተሰጠው መረጃ ሃሰት መሆኑን በመግለጽ ከሳሽን አግዶ በ26/7/2014ዓም አሳውቋል። ከሳሽ የሰጠው ሃሰተኛ መረጃ የለም እንጂ ቢኖር እንኳ ተከሳሽ በአዋጁ አንቀጽ 98(2) መሰረት ከሳሽ እንዲያስተካክል እድል ሳይሰጥ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ ቁጥር 98(3) መሰረት ከሳሽ መከላከያውን አቅርቦ እንዲያሰማ ሳያደርግ የእግድ ውሳኔ ከህግ ውጪ ያስተላለፈ በመሆኑ ተከሳሽ ከህግ ውጪ ያስተላለፈውን የእግድ ውሳኔ ህገ ወጥ መሆኑን በማረጋገጥ የእግድ ውሳኔው እንዲነሳ ተወስኖ ለሚመለከታቸው አላላት ውሳኔው እንዲተላለፍ እንዲሁም የክርክር ወጪውን ተከሳሽ እንዲሸፍን ይወሰንልን በማለት ጠይቋል። ለማስረጃነትም ሰነዶችን አያይዞ ምስክሮችን ቆጥሯል።

ለከሳሽ ክስ ተከሳሽ በሰጠው በ25/ 9/ 2014ዓም በተጻፈ መልስ ከተከሳሽ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 6 መሰረት የተከሳሽ ስልጣንና ተግባር ውስጥ የፐለቲክ ፓርቲዎችን መመዝገብ፤ መከታተል ና መቆጣጠር መሆኑን፤ አንድ የፖለቲካ ፓርቲም ምዝገባ ሲያከናውን ማናቸውንም የውሳ አሰጣጥ ሂደቱ ህግና የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ባደረገ በተከሳሽ ጥብቅ ቁጥጥር እና ክትትል እንደሚደረግበት አውቆ እንደሆነ፤ በአዋጅ 1162/2011 አንቀጥ 79(2) መሰረት ተከሳሽ የከሳሽን ስብሰባ ታዝበው ሪፖርት እንዲያቀርቡ የላካቸው ባለሙያዎች ባቀረቡት ሪፖርት ጠቅላላ ጉባኤው በፓርቲው መተዳደሪየ ደንብ መሰረት ለተከሳሽ ያቀረቡት ዝርዝር ሪፐፖርት ጉባኤው በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መስት ምልአተ ጉባኤ ሳይሟላ መደረጉን ማረጋገጡን፤ በማስፈረሚያ ሰነዱ እና በጉባኤው ላይ በተገኙ አባላት መካከል ልዩነት

በመፈጠሩ ለስብሰባ አደራጆች ችግሩ እንዴት እንደተፈጠሩ በጠየቁት ማብራሪያ የተሰጠው ምላሽ ማስፈረሚያ ሰነዱ ለአባላት ቀደም ብሎ ተልኮ የተፈረመ መሆኑ እንደተገለጸላቸው ለተከሳሽ በሪፖርት በመገለጹ በከሳሽ የቀረበው ሪፖርት እርእር ሁኔታው የሚመለከተው መረጃ እንዲሁም ለተከሳሽ ጠቅላላ ጉባኤን አስመልክቶ የቀረቡለት ሰነዶች ምልአተ ጉባኤ መሟላትን በሚመለከት የቀረበው ጉባኤው 634 አባላት ተገኝተው የተደረገነው ሲል የገለጸበት ሰነድ ትክክለኛ መሆኑ አጠራጣሪ የሆነ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጥ 79(3) መሰረትም ሀሰተኛ መሆኑን ተከሳሽ ሲያረጋግጥ በአንቀጥ 98 መሰረት እርምጃ እንደሚወስድና ፓርቲውን እንዲሁም በድርጊቱ የተሳረፉ ግለሰቦችን በወንጀል ዕምር ተጠየቂ ማድረግ እንደሚችል ህጉ የሚደነግግ በመሆኑ ይህንኑ ለማረጋገጥ የምርመራ ሂደት የተጀመረና ውጤቱም እስኪታወቅ በአንቀጥ ቁጥር 98(3) መሰረት የእገዳ ውሳኔ ማስተላለፉ ህግን መሰረት ያደረገ እርምጃ ነው ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግ በማለት ጠይቆ መልስ ሰጥቷል፡፡ ለማስረጃነትም ሰነዶችን አያይዞ ምስክሮችን ቆጥሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ያደመጠ ሲሆን የጽሁፍ ክርክራቸውን አጠናክረው አሰምተዋል፡፡ ከክርክሩም ተከሳሽ በከሳሽ ላይ የሰጠው የእገዳ ውሳኔ ህጉን ያልተከተለና ሊሰረዝ የሚገባው ነው? አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመለየት ከህጉ ጋር በማገናዘብ እንዲመከተለው መርምሯል፡፡

ከሳሽ በክሱ በክሱ የተመለከተውን የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በህጉ ከሚጠየቀው የአባላት ብዛት በላይ የሆኑና በቁጥር 634 የሆኑ አባላት መገኘታቸውን በማረጋገጥ የተደረገውን የጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ለተከሳሽ ማቅረቡን፤ ይህ የቀረበው ሪፖርትም ትክክለኛ መሆኑን፤ ትክክለኛ አልነበረም ቢባል እንኳ ተከሳሽ በቅድሚያ ለከሳሽ ይህንን እንዲያስተካክል ማስጠንቀቂያ መስጠት እንዲሁም መከላከያውን አቅርቦ እንዲያሰማ ማድረግ ሲኖርበት ይህንን የህግ ግዴታ ሳይወጣ የእገዳ ውሳኔ ያስተላለፈው ከህግ ውጪ ነው፤ ለተከሳሽ ባቀረበው የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ሪፖርት ላይ በጠቅላላ ጉባኤው የተገኙ አባላት ቁጥር 634 የተባለው የተሳሳተ መረጃ

እንዳልሆነ፤ ሆኖ ቢሆን እንኳ ተከሳሽ ከሳሽ ይህንን እንዲያስተካክል እድል ሊሰጥ ይገባ እንደነበር፤ በተጨማሪም ከሳሽ ማስረጃውን በማቅረብ እንዲከላከል ሊፈቅድ ሲገባ የእገዳ ውሳኔ መስጠቱ ህጉን የተከተለ እንዳልሆነ ገልጾ ተከራክሯል። ተከሳሽ በበኩሉ ከሳሽ ለተከሳሽ ጠቅላላ ጉባኤውን አስመልክቶ የሰጠው መረጃ ትክክለኛነት አጠራጣሪ መሆኑን በራሱ በተከሳሽ ተወካይ ባለሙያዎች በቀረበው ሪፖርት ማረጋገጡን፤ በዚህ ምክንያትም በከሳሽ የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሞ ነበር ወይ የሚለውን ተጣርቶ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ፓርቲው ላይ የእገዳ ውሳኔ መስጠቱ ህግን መሰረት ያደረገ እርምጃ ነው ሲል ተከራክሯል።

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል። የግራ ቀኙ ክርክር ከሳሽ ጠቅላላ ጉባኤውን 634 አባላት በተገኙበት አከናውኗል የሚል ሲሆን ተከሳሽ ደግሞ ከሳሽ ጠቅላላ ጉባኤውን ተካፍለዋል ሲል የሰጠው መረጃ ና ሪፖርት ሃሰተኛ እንደሆነ በተወካዮቹ የተገለጸለትን ይህም አጠራጣሪ ሆኖ ያገኘው በመሆኑ ይህንን እስኪያጣራ ድረስ ከሳሽ ላይ የእገዳ ውሳኔ መስጠቱን ገልጧል። ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር ከሳሽ ስለጠቅላላ ጉባኤው መረጃ ለተከሳሽ መስጠቱን፤ ተከሳሽም ከሳሽ በሰጠው ይህ መረጃ ትክክለኛነት ላይ አጠራጣሪ ሁኔታ አለ ብሎ ማመኑን መመልከት ይቻላል።

በኢትዮጲያ የምርጫ ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 98 ተከሳሽ ቦርድ አንድ የፖለቲካ ፓርቲን ከምዝገባ ሊሰርዝ ስለሚችልበት ምክንያቶች ይደነግጋል፡፤ ከምክንያቶቹ አንዱ በአንቀጽ 98(1ሠ) ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተከሳሽ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲው የሀሰት መረጃ ለቦርዱ የሰጠ እንደሆነ ካረጋገጠ የፖለቲካ ፓርቲውን ሊሰርዝ እንደሚችል ፤ ሆኖም ከስረዛው በፊት ወይም በቅድሚያ በአንቀጽ 98(2) መሰረት የፖለቲካ ፓርቲው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስህተቱን እንዲያርም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው እንደሚገባ ሲደነግግ አንቀጽ 98(3) ደግሞ ቦርዱ የስረዛ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት ፓርቲው መከላከያውን አቅርቦ እንዲሰማ ሊያደርግ እንደሚገባ ያስቀምጣል። ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲውን ከምዝገባ ከመሰረዙ በፊት ፓርቲው ታግዶ እንዲቆይ ሊወስን

እንደሚችል ይህው አንቀጽ ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተከሳሽ በቁጥር አ1162/11/574 በ23/7/2014ዓም የሰጠው የቦርድ ውሳኔ ስንመለከት አንድ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባምልአተ ጉባኤ የሚሟላው ቢያንስ 500 የጉባኤ አባላት ሲገኙ እንደሆነ መደንገጉን፤ ሆኖም ከሳሽ ባካሄደው ላይ የተገኙት 250 አባላት ብቻ መሆኑን ፤ ስብሰባው በህጉ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ምልአተ ጉባኤ ሳይሟላ የተካሄደ ስብሰባ እንሆነ ከተከሳሽ ተወካዮች ማረጋገጡን፤ ከሳሽ ግን በ22/7/ 2014ዓም ለተከሳሽ ባቀረበው ሪፖርት 634 አባላት ተገኝተዋል በማለት የስም ዝርዝርና ፊርማ ለተከሳሽ ማቅረቡን ይህ ሁኔታም ከሳሽ ፓርቲ ለቦርዱ ያቀረበው የስም ዝርዝርና ፊርማ ሃሰተኛ መሆኑ እንዳጠራጠረው፤ ቦርዱ ተጨማሪ ማጣራት እስከሚያካሂድ ድረስ ፓርቲው ከ23/7/ 2014ዓም ጀምሮ እንዲታገድ መወሰኑን ይገልጻል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 98(3) ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲውን ከምዝገባ ከመሰረዙ በፊት የማጣራት ሂደቱን እስኪያጠናቅቅ ድረስ ፓርቲው ታግዶ እንዲቆይ ሊወስን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ከሆነ ተከሳሽ ቦርድ ከሳሽ የፖለቲካ ፓርቲን ሊሰረዝ ይገባል አይገባም የሚለው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ፓርቲውን ሊያግድ እንደሚችል ህጉ የሚያስቀምጥ በመሆኑ የተከሳሽ የእግድ ውሳኔ ህጉን የተከተለ አይደለም ፤ ከህግ ውጪ ነው የሚባል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሆኗል፡፡

ግራ ቀኙ የክርክር ወጪያቸውን ይቻቻሉ፡፡

ይግባኝ መብት ነው፡፡ መዝገቡ በውሳኔ የተዘጋ በመሆኑ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የዳኛ ፊርማ አለው፡፡